# በፌስ-ቡክ መድረካችን ላይ
# በሰኔ ወር፥ ፳፻፰ ዓ. ም. ለቀረቡ ጥያቄዎችና ትችቶች፡
# ከኢእመ የተሰጡ መልሶች። ፫ኛ።

**ከWondish Leul የተሠነዘረ የነቀፋና የዘለፋ ትች፡-**

*AYYyyyyy tiliku sewuye leka eskahun mishig yizeh yihen yekihidet kal eyezerah new ENAT BETEKRSTIANIN eyasedebkina yalhonechiwun yalastemarechiwun endebedelina kifu timhirt kotrew leloch afachewun endikeftu yemtadergewu. Baynekabih noro gud serteh neber ahun gin maninetihina sirah siletenekabih kezih behuala maninim atatalilim!!!!!!!!!!!!*

**የኢእመ መልስ፡-**

ይድረስ፡- ለወይዘሪት/ወይዘሮ ወንድሽ ልዑል!

ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ በእግዚአብሔር ስም እያቀረብንልዎ፡ በፌስ-ቡክ ጎዋ መድረካችን ላይ ስለሠነዘሩት የነቀፋና የዘለፋ ትች፡ የምንሰጥዎ መልስ፡ "እግዜር ይስጥልን!" ከሚለው አጻፋችን ጋር፡ ባጭሩ፡ ከዚህ የሚከተለው ነው።

እርስዎ፡ "እናት ቤተ-ክርስቲያን" የሚሏት፡ የትኛዋን ነው? የእርስዎን? ወይስ፡ የእኛን? ወይስ፡ የዛሬ ፫ሺ፰ ዓመታት፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ የቅኝ ቀንበር ሥር ወድቃ፡ እየማቀቀች ያለችውን፥ ደግሞም፡ የዛሬ ፩ሺ፯፻፰ ዓመታት፡ በ፬ኛው የክርስትና ምእት-ዓመት ላይ፡ በግብፃውያን መነኮሳት፡ በኢትዮጵያ ምድር እንደተቋቋመች፡ ራሷ አምና፡ ሌሎችንም ለማሳመን የምትጥረውን፣ ራሷንም፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን!" ብላ የምትጠራውን ነወይ፡ እርስዎ፡ "እናት ቤተ-ክርስቲያን" የሚሏት?

ይህችን ከኾነ፥ ይህችው ቤተ-ክርስቲያንማ፡ በኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ የምትታወቀው፡ "በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቅርንጫፍ" ተብላ መኾኑን፡ በቅድሚያ፡ ይህን እውነታ እንዲገነዘቡት ልናሳስብዎ እንወድዳለን።

በመቀጠል ደግሞ፡ ሊያውቁት የሚገባዎት እውነታ፡- **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ፡ ከፍጥረተ-ዓለም ጀምሮ ያለውንና ፍጹም የእግዚአብሔር ብቻ የኾነውን፡ እውነተኛውን ዘለዓለማዊና ክህነታዊ የአስተምህሮ ተልእኮዋን፡ እነሆ እስካኹን፡ ለ፯ሺ፭፻፰ (ለሰባት ሺህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት እያበረከተች ያለችው፡ የእኛ "እናት ቤተ-ክርስትያን"፡ "የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን" ተብላ የታወቀችው መኾኗን ነው። እርሷም፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ መንፈሳዊዉን አገልግሎት፡ ለሕዝቧ እንዲያበረክት፡ በቤተ-ሕዝቧ የተሠየመው፡ ራሱ ቤተ-ክህነቱ ናት። ሥጋዊዉን አገልግሎት፡ ለሕዝቧ እንዲያቀርብ፡ በቤተ-ሕዝቧ እንደተሠየመው፡ እንደቤተ-ምልክናው ዘርፍ ማለት ነው።

ለመኾኑ፡ እርስዎ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፥ በእምነቷና በትምህርቷም ያምናሉ? የማያምኑ ከኾኑ፥ ወይም፡ ስለእርሷ፥ ስለእምነቷና ስለትምህርቷም፡ በቀጥታ፡ ከእርሷው ለማወቅ የማይፈልጉ ከኾኑ፡ ለምን፡ ወደዚህ፡ የፌስ-ቡክ መድረካችን በመምጣት ይደክማሉ? ለምን፡ እዚያው፡ በሚከተሉትና አባል በኾኑበት የሃይማኖት ድርጅትዎ አይወሰኑም?

በዚህ ረገድ፡ የእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ ልጇ ወዳጇ፣ የእኛም የኪዳናውያትና የኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆች መሪና መምህር የኾነው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ስለእርስዎና እርስዎን ስለመሰሉት ኹሉ፡ እንዲህ ሲል የተናገረውን ሰምተዋል? አንብበዋል? **"ዘሰ እምእግዚአብሔር ውእቱ፡ ቃለ-እግዚአብሔር ይሰምዕ። ወበእንተ ዝንቱ፡ <u>አንትሙሰ፡ ኢትሰምዑኒ፤ እስመ ኢኮንክሙ እምእግዚአብሔር።</u>**

"ከእግዚአብሔር የኾነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል። <u>እናንተ ግን፡ ከእግዚአብሔር ስላልኾናችሁ፡ ስለዚህ፡ አትሰሙኝም።"</u> (ዮሐ. ፰፥ ፵፯።)

አዩ! <u>የእኛ እናት ቤተ-ክርስቲያን፡</u> ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸልዎ፡ ዘንድሮ፡ ለ፯ሺ፭፻፰ ዓመታት ዕድሜዋ በበቃችው፥ የእግዚአብሔር መንግሥትና እናት አገራችን በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት የተገለጠችው ኢትዮጵያ ናት።

ይኹን እንጂ፡ እርስዎ፡ በእርግጥ፡ ስለእግዚአብሔርና ስለኢትዮጵያዊነት እውነት፡ የማወቅ ፍላጎት ካለዎ፥ ያም ፍላጎትዎ፡ እውነተኛ ከኾነ፡ ያን ፍላጎትዎን፡ በበለጠ ሊያረኩ የሚችሉበት መንገድ አለልዎ፤ ይኸውም፡ እንዲህ፡ በእርስዎና በመሰሎችዎ ዘንድ፡ ሊኖር ለሚችለው፡ ለዚህና ለሌላው፡ እጅግ ብዙ ለኾነው፡ የተያያዘ ጥያቄና ትች ኹሉ፡ አጥጋቢ መልስና በቂ ማብራሪያ ኾኖ፡ በጽሑፍ የተሰጠው ዝግጅታችን፡ በጎዋ ሰሌዳችን፥ እንዲሁም፡ በፌስ ቡክ፥ በዩ-ቲዩብና በሳውንድ-ክላውድ መድረኮቻችን፥ ዝርዝራቸውም፡ በእነርሱ ላይ ሠፍሮ በሚነበበው መጽሓፎቻችን ውስጥ ስለሚገኝ፡ ያን ዝግጅታችንን እንዲመለከቱ እንጋብዝዎታለን።

ይህን የጨዋነት ምግባር በመፈጸም፡ የእርስዎን ብቻ ሳይኾን፡ የእኛንም ውድ ጊዜ ሊያድኑልን ይቻልዎታል።

እስከዚያው፡ እስኪ ጥቂት ማብራሪያና ምዕዳን እናክልልዎ! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርስዎንና እርስዎን የመሰሉትን ሰብአውያንና ሰብአውያት ፍጡሮቿን በሚመለከት፡ የምታስበውና የምታደርገው ምን እንደኾነ፥ አኹንም፡ እንዲህ እየደከመች ያለችው፡ ለምን እንደኾነ ያውቃሉ? ባጭር እንግለጥልዎ!

በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ላይ የተመሠረተውንና ከዚያ የሚመነጨውን መልእክቷን፡ በቃል ብቻ ሳይኾን፡ በመጻሕፍቷ፥ እንዲሁም፡ በጎዋ ሰሌዳዋና በፌስ-ቡክ፥ በሌሎቹም የሕዝብ መገናኛዎች በኾኑት ጎዋ አውታሮቿ አማካይነት፡ እንዲህ፡ በማሠራጨት የምትደክመው እኮ፡ እናንተ፡ "የእኛ" ስለምትሏት፡ ስለዛሬዋ፡ የ"ጳጳሳት" እና የመነኮሳት ድርጅት፥ ስለእናንተም፡ ስለእየራሳችሁ ምንነትና ማንነት፥ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮት፥ በእነዚህም ጥበብና ኃይል፡ በበለጠ ግልጥነትና በአማናዊው ትክክለኛነት እንድታውቁት ለማድረግ ነው።

ይህን እግዚአብሔራዊ ዕውቀት በምታገኙበት ጊዜ፡ ምን ዓይነቱ የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ትንግርት እንደሚከሠት፡ እናበሥርዎ ዘንድ ይወድዳሉ!? ከወደዱ፡ ይኸውልዎ! ይኸው፡ የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ትንግርት፡-

በቅድሚያ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ወገኖች፡ በዚያ፡ በተቀዳጃችሁት፡ እግዚአብሔራዊ ዕውቀት፡ እየራሳችሁን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ የምታበቃችሁ፡ የፍጹሟ ንስሐ፡ ፍሬያማ ባለቤቶች ትኾናላችሁ።

በማስከተል፡ "የእኛ እናት ቤተ-ክርስቲያን" የምትሏት፡ የዛሬዋ፡ የ"ጳጳሳት" እና የመነኮሳት ድርጅት፡ እናንተ፡ እየራሳችሁ ስለኾናችሁ፡ የእናንተ፡ በእውነተኛ ንስሐ፡ ወደእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት መመለስ፡ እርሷንም፡ ወደቀደመችዪቱ፣ ጥንታዊቷና እውነተኛዪቷ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መንፈሳዊ ዘርፍ ወደኾነችው፡ ወደኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያንነቷ ትመልሷታላችሁ።

"አያድርስ!" እንጂ፡ ምናልባት፡ ባለመታደል፡ በእናንተ በኩል፡ ይህ ሳይኾን ቢቀር ግን፡ በእርግጥ የሚኾነውን፡ ለእርስዎም፥ ለመሰሎችዎም እናርዳችሁ! ይኸውም፡-

በመጀመሪያ፡ በጌታችን በኢየሱስ መሲሕ፡ መለኮታዊ ቃል፡ **"አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ! ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ፤ ...ወውእቱሰ፡ ሐሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሓ ለሐሰት!"**

"እናንተማ፡ የአባታችሁ፡ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ! ስለዚህ፡ የእርሱን፡ የአባታችሁን ፍላጎት መፈጸምን ነው፡ እናንተም የምትፈቅዱት! ...እርሱ ጥንቱኑ ሐሰተኛ፥ የሐሰትም አባት ነው።" እንደተባሉት፡ እንደአሪታውያኑ ጌቶቻችሁ፡ እንደአይሁድ፡ እናንተም፡ የኢትዮጵያ ልጆች መኾናችሁን በመካድ፡ እንደእነርሱ፡ አሪታውያን አይሁድ መኾንን መምረጣችሁ ነው፤

ኹለተኛም፡ በዚህ እምቢተኛነታችሁና አንገተ ደንዳናነታችሁ፡ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር እና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ላይ፡ ለዝንተ-ዓለም፥ በተለይም፡ በእርስ-በርስ ደም-መፋሰስና የዕልቂት ጦርነት የተመላው፡ የህልውና ዘመናችሁ፡ ይኸው ዛሬ፡ "ለሦስት ሺህ ስምንት ዓመታት በቃ!" እያላችሁ፡ በሚያሳፍር እልህ እየፈጸማችሁ ባላችሁት፡ የዓመፀኛነታችሁና የክህደታችሁ፥ የክፋታችሁና የአምልኮ አመንዝራነታችሁ ኃጢአት ምክንያት፡ ፈጽማችሁ፡ ጠፍታችሁ የምትቀሩ መኾናችሁ የተረጋገጠበትን፡ የእግዚአብሔርን እውነት ዐውቃችሁ፡ በፍላጎታችሁና በምርጫችሁ መቀበላችሁ ነው። (ዮሐ፣ ፰፥ ፵፬።)

ይህ፡ የእግዚአብሔር እውነታና የማይቀረው ተፈጻሚነቱ፡ እንዳለ ኾኖ፡ ይህችው፡ እናንተ፡ "እናት ቤተ-ክርስቲያናችን!" የምትሏት፡ የ"ጳጳሳት" እና የመነኮሳት ድርጅት፡ **እንግዴህ ወዲህ፡** <u>ሰብአዊውና ሰይጣናዊው ገመናዋ፡</u> እየተጋለጠና እየጠራ በመኼድ ላይ ያለው፡ በእነማን እንደኾነ ያወቁና ያስተዋሉ አልመሰለንም። በእኛ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆችና አገልጋዮች ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በራሳቸው፡ በባለቤቶቿ፡ በእናቲቱ፡ **በእግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም እና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ መሪነትና የዐዋጅ ነጋሪነት ነው።** እስካኹን፡ ካላወቁና ካላስተዋሉ፡ ከአኹን ጀምረው ይወቁት! ልብ ብለውም፡ ያስተውሉት!

\+ \+ \+

**ከኪዳናዊ ፋሲካ መኰንን የቀረበ ጥያቄ፡-**

*ይድረስ፡- ለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት አገልጋይ ለሆንከው ለኪዳናዊ ወንድሜ ንቡረእድ ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ፤ ለጤናህ እንደምን ከርመሃል? እኔ ልዑል እግዚአብሔር ከነእናቱ የተመሰገነ ይሁን ደህና ነኝ።*

*በምትሰጠው አገልግሎት የማያቋርጥና ምክንያታዊ መልስ እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ። በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት አገልግሎት ውስጥ ካስተማሩኝና ከምኮራባቸው ሂደቶች መካከል ማንኛውም ሰው የመሰለውን ጥያቄ መጠየቅ መቻሉ እና ለጥያቄዎች ሁሉ ተገቢ መልስ መኖሩን የተረዳሁ እለት ትልቁን ደስታ ያገኘሁበት እለት ነው ማለት እችላለሁ። ምክንያቱም ያልተለመደ ነገር ነበርና ነው።*

*ከዚያም አንፃር ለዛሬ መጻሕፍትን ስመረምር ካጋጠሙኝ መካከል አንዲት ጥያቄን ይዤ መጥቻለሁ። ለጥያቄዬም አጥጋቢ መልስ እንደምትሰጠኝም አምናለሁ። ምናልባትም መጻህፍትን ከመመርመር የተነሳ ጥያቄዎች ይነሳሉና የኔም ሃሳብ ሰሞኑን ሳነብ ካጋጠሙኝ መጽሐፍቶች ያነበብኩትን ይመለከታል።*

*የመጽሐፉ ርዕስ "ሚስጥረ [ምስጢረ] ሰማያት ሚስጥረ [ምስጢረ] ኢትዮጵያ ፍልስፍና" ይሰኛል። የተፃፈውም ጤንነት ሰጠኝ በተባሉ ጸሐፊ ሲሆን መጽሐፉ የሚያትተው ፍሬ ነገርም በሰማየ ሰማያት በነበሩ ፍጥረታት መካከል ማለትም በአንበሳ አምሳል፣ በንስር፣ በላም እና በሰው አምሳል በተፈጠሩ ኀያላን መካከል ስለተደረገ ከፍተኛ ጦርነት ይናገራል። ከጦርነቱ በኋላም በተለይ የገዢነት ክብራቸውን ጠብቀው ባሉት እንስሳትና ሰዎችን ጨምሮ እና ባልጠበቁት መካከል በሚል" በጥልቀት የተብራራና የሰው ልጆች እጣ ፈንታ የሚወሰነው በአራት አቅጣጫ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ እና በምዕራብ አቅጣጫ በሰማየ ሰማያት ባሉት ኀያላን እንስሳት እና መላእክት በሰዎች የነፍስ ባህሪያት ልባዊት፣ ሕያዊትና ነባቢት ላይ ባላቸው ስልጣን የሰው ልጆችን ነፍስ ተጠግተው እንደሚያስተምሯትና በተለይ ከእነርሱ ፍላጎትና ተፅዕኖ ውጭ የሰው ልጅ ምንም ዓይነት ለውጥ ማምጣት እንደማይችል ያትታል።*

*ያም ማለት በላም፣ በአንበሳ በንስርና እና በሰው በተመሰሉት ገዢዎች ተፅዕኖ ስር ያሉት ሰዎች የሚያደርጉት የገዢዎቻቸውን ፍላጎት እንጂ የእራሳቸውን አይደለምና በሶስቱ ቦታ ያሉ የገዢዎቻቸው ፈቃድ ደግሞ ከእግዚአብሔር ፈቃድ የወጣ እና መጨረሻውም የጥፋት እና የስህተት ነው ይላል። ከአንዱ በንስር ከሚመሰለው በስተቀር፡ በተጨማሪም የሰው ልጅ ነፃ ፈቃድ እንደሌለውና የገዢዎቹን ፍላጎት ብቻ ሲያሟላ የሚኖር ፍጡር እንደሆነ በዝርዝር ተፅፎ ይነበባል። በተጨማሪም፡ በሰማየ ሰማያት እና በምድራዊ ሰማያት በሚደረገው የማያቋርጥ የድግግሞሽ ሂደትን የሰው ልጆች ፈለጉም አልፈለጉ የገዢዎቻቸውን ፍላጎት እንደሚያደርጉት የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው።*

*ለመሆኑ ይሄን አይነት ትምህርት በተለይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተፅፎ የሚገኝ ትምህርት ነው። ብዙ ሰዎችም ይሄ ትምህርት እውነት እንደሆነ ሲናገሩና በሚስጥር [በምስጢር] ሲያስተምሩ ይስተዋላል። የሰው ልጆችም እጣ ፈንታቸውን ማስተካከል እንደማይችሉና በተለይ ንስሓን በተመለከተ እስከዛሬ ድረስ ስታስተምረን የነበረውን ሃሳብ ፍፁም የሚቃወም ትምህርት በማግኘቴ፡ በተለይ ይሄ አይነት ትምህርት ለቤተክርስትያን ቅርብ ከሚባሉ ሰዎች መገኘቱ ከባድና ግራ የሚያጋባ ሁኔታን የመፍጠር አቅም ይኖረዋል።*

*እና "እውነት የሰዎች ልጆች የሚፈልጉትን በነፃ ፈቃዳቸው ያደርጋሉ? ወይስ የገዢዎቻቸውን ፈቃድ በተጽዕኖ ያደርጋሉ?" የሚል ጥያቄም ያስነሳል። በእርግጥ እኔ፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት አገልግሎት ስር በኪዳናዊነት የምኖር ሲሆን፡ ጥያቄውን ማንሳቴ እንደአጠቃላይ ግንዛቤን ለማግኘት ነውና ምናልባት አንተን በማይረባ ጥያቄ ጠቃሚ ጊዜህን እንዳላባክንብህ እሰጋለሁ። እናም እባክህ፡ ስለዚህ ሁኔታ የምታውቀውን መልስህን እንደተለመደው እናፍቃለሁ።*
*አክባሪ ኪዳናዊ ወንድምህ ፋሲካ መኮንን ከናዝሬት።*

**የኢእመ መልስ፡-**

ይድረስ፡- ለኪዳናዊ ወንድሜ ፋሲካ መኰንን።

እግዚአብሔር አብወእም፡ በቅዱስ መንፈሳቸው፡ አንተንም፥ እኔንም፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች የኾንነውን ኹላችንንም፣ ከነቤተሰቦቻችን፡ በእያለንበት ስለሚጠብቁንና ስለሚመሩን፡ እናመሰግናቸዋለን።

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለማበረክተው የማያቋርጥ አገልግሎት፥ ለቀረቡ ጥያቄዎችም፡ ስለምሰጠው ምክንያታዊ መልስ፡ የላክህልኝን፡ የ"እግዚአብሔር ይስጥልኝ!" ምርቃትህን፡ በአክብሮት ተቀብዬ፣ እኔም፡ በዚሁ መልክ፡ ሰላምታዬንና ምርቃቴን፡ ይኸው ሰድጄልሃለሁ።

ብዙዎቹን ጥያቄዎቻችንን፡ በውስጣችን ያለው እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ፡ የተሟላውን በቂ መልስ የሚሰጠን መኾኑን ብናውቅና ብናምንበትም እንኳ፡ "እኔው አስተምራቸዋለሁ!" ያለውን መለኮታዊ ቃሉን በመዳፈርና በመተላለፍ ሳይኾን፡ በመጠበቅና በማጽናት፡ አንዳንድ ጊዜ፡ እጅግ አስፈላጊያችን ኾኖ ስናገኘው፥ የዕውቀታችንን ትክክለኛነት ለማረጋገጥና ስለአንዳንድ ቍም-ነገሮች፡ በበለጠ ለመረዳት፥ ደግሞም፡ በእግዚአብሔራዊው ዕውቀታችን እየጐለመስንና እየተጠናከርን ለማደግ፡ እርስ በእርሳችን ብንጠያየቅ፡ ይበጃል እንጂ፡ አይጎዳንምና፡ አኹን፡ ይህን ጥያቄ፡ ለእኔ በማቅረብህ፡ "ምናልባት፡ ጠቃሚ ጊዜውን አባክኜበት ይኾን?" የሚለውን ሥጋትህን እንድታስወግደው፡ በቅድሚያ አሳስብሃለሁ።

በኪዳናዊነትህ እንደምታውቀው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በቀጥታ ከፈጣሪዋ ተቀብላ፥ እነሆ ዛሬ፡ ለ፯ሺ፭፻፰ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ-ቅዱስ አምልኮዋ ጠብቃና አጽንታ ያኖረችው፣ የተመሠረተችበትና የያዘችው፥ የምትኖርበትና የምታካኺደው፡ ሕይወቷና ህልውናዋ፥ እውነቷና እምነቷ፥ ዕውቀቷና ትምህርቷ የኾነ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት አላት።

ያም ሃይማኖት፡ ከልደተ-ዓለማቱ፡ ማለትም፡ ከፍጥረት በፊትና በኋላ፡ በመለኮታዊው መንፈስ ሲሠራ የቆየው፥ በመጨረሻው፡ የሕይወት ዘመንም፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና በልጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት ተከሥቶ የታየው፥ የተነገረውና እውን ኾኖ የተፈጸመው፡ እግዚአብሔራዊ አሳብና ቃል፥ ምግባርና ሥርዓት ነው።

እርሱንም፡ ሌሎቹ፡ በመላው ዓለም የሚኖሩ፡ የሰው ወገኖች ኹሉ፡ ሰይጣናዊና ሰብኣዊ በኾነው፡ ረቂቅ ኾነ ጉልህ ስልትና ዘዴ አማስነው [አበላሽተው]፡ ለዓለማዊውና ለምድራዊው፥ ለሥጋዊዉና ለፍልስፍናዊው ጥቅማቸው ሲያውሉት፡ እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ግን፡ በብቸኝነት አምነንባት፡ በልጅነት፥ በነጋሢነትና በካህንነት የምናገለግላት፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርሷ ብቻ፡ ይህንኑ እግዚአብሔራዊ ሃይማኖት፡ ሳትለውጥና ሳትበርዝ፥ ሳትጨምርና ሳትቀንስ፡ በፍጹም ንጽሕናውና ጥራቱ፡ እንዳለ ጠብቃና አጽንታ አኖራዋለች፤ ዛሬም፡ በዚሁ አቋሟ ጸንታ ትገኛለች፤ ወደፊትም፥ ለዘለዓለም ትቀጥልበታለች።

ይኸው እግዚአብሔራዊው ሃይማኖታችን፡ በአራቱ፡ ማለትም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የሃይማኖትና የቃል ኪዳን፥ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎቶቻችን ውስጥ ተካትቶ ይገኛልና፡ ያንን፡ ከመጻሕፍታችን እያገላበጡ፥ ከጎዋ-ሰሌዳችንም እየከፈቱ መመልከት ነው።

ለመኾኑ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ሀገረ-ማርያም በኾነችው፡ ኢትዮጵያዊት ቅድስት ምድር ላይ፡ በአምልኮተ-እግዚአብሔር ርስት-ጕልትነት ፍቅር፡ በሰላምና በደስታ የሚኖረውን፡ ሕዝበ-እግዚአብሔር የኾነውን ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ወገን፡ ይኸው፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ከእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮው እያናወጹትና ለባዕድ አምልኮ እየዳረጉት፡ ግራ ሲያጋቡትና ከቅዱሱ ቍርባን ሲያርቁት፥ ከዚህ የተነሣም፡ የእንስሳትን ብቻ ሳይኾን፡ በበለጠ፡ ከነሥራዊቱ፡ የሰዎችን ደም መጠጣት የሚወድደው ዲያብሎስ፡ በማያቋርጥ ጦርነት፡ ይኸው እስከዛሬና ዛሬም፡ እርስ በርሱ እያዋጋ፥ ደም እያፋሰሰና እያጋደለ እንዲኖር ያደረጉት እነማን ናቸው?

አኹን አንተ፡ ኪዳናዊው ወንድሜ፡ ይህን የመሰለውን ጥያቄ እንድታቀርብበት ያስፈለገህን ዓይነት፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ኢትዮጵያ የኾነ፡ ሰይጣናዊና የባዕዳን አስተሳሰብና እምነት እያመጡ፥ በመካከሉም እያሠራጩ ያሉት፡ "ቤተ-ክርስቲያን ነን!" እስከማለት የደረሱት፡ የሃይማኖትና የመነኮሳት ድርጅቶች አይደሉምን? አዎን! በእርግጥ፡ እነዚህ ናቸው።

ስለዚህ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከፈጣሪዋ፡ አግኝታ፡ ለእኛ ለልጆቿ ያስረከበችንን፥ የቀደሙት ምዝላቶቻችንና እኛም አጽንተን ጠብቀን ያቆየነውን፡ ይህን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን፡ ለእየራሳችን ሕይወት አድርገን ከመኖርና እንደመምህራችን ኢየሱስ መሲሕ መመሪያ፡ ምሥራቹን፡ በሓዋርያነታችን፡ ለመላው ዓለም ሰዎች ከማሰማትና ከማዳረስ በቀር፡ እርሷም፥ እኛ፡ ልጆቿና አገልጋዮቿም ብንኾን፡ የእነዚህን፡ "ቤተ-ክርስቲያን" ተብዬዎችና የሃይማኖት ድርጅቶች አስተምህሮ፡ ፈጽመን አንቀበለውም።

ቍጥራቸው፡ እጅግ ብዙ ስለኾነው፡ ስለእነዚህና ስለሌሎች ባዕዳን ሃይማኖቶች፡ ይህን በመሰለው መድረካችን ላይም ቢኾን፡ በመጠያየቅና በመነጋገር፡ የአእምሮ ሀብታችንንና ዓቅማችንን፥ ውድና ሰላማዊ ጊዜያችንንም፡ በከንቱ ማባከን የሚያስፈልገን አይመስለኝም። ምናልባት ካስፈለገን፡ ለእየራሳችን ለማወቅ ያህል፡ አንተም እንዳደረግኸው፡ በየግላችን ማንበቡና እርስ በርሳችን፡ በግል መወያየቱ የሚበቃ ይመስለኛል።

ለዚህ እኮ ነው፡ በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቅርንጫፍ የኾነችውንና ራሷን፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን" ብላ የምትጠራውን፡ የ"ጳጳሳት" እና የመነኮሳት ድርጅት እንኳ ሳይቀር፡ ጠንቀኞቹና የሦስት ሺህ ዓመታት ገዢዎቿ አሪታውያኑ አይሁድና ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች ከጫኑባት ግብስብስ ይትባሃሎቿ ጋር፡ ለእነርሱና የእነርሱ ተከታዮች ለኾኑት ትተን፡ እኛ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም መቅደስነትና ንግሥትነት፥ እንዲሁም፡ በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ካህንነትና ንጉሥነት የምትመራውን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን ብቻ ተከትለን የምንኖረውና የምናገለግለው።

ይህችኑ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን** ብቻ፡ ተከትለን የምንኖረውና የምናገለግለውም፡ እንዲያው በከንቱ፥ ያለበቂ ምክንያትም አይደለም፤ መምህራችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በሕይወተ-ሥጋ ዘመኑ፡ ከእርሱ ጋር ለነበሩት፣ እንዲህ እንደዛሬው ትውልድ ኹሉ፡ ማስተዋል ለተሳናቸውና እምነት ለጎደላቸው ደቀ መዛሙርቱ፡ የሰጣቸውን መመሪያ ቃሉን፡ አምነን በመፈጸም ነው እንጂ። ቃሉም፡ እንዲህ የሚል ነው:-

<u>"ዑቁ፥ ወተዐቀቡ፡ እምብኁአሙ ለፈሪሳውያን፥ ወለሰዱቃውያን!</u>

"ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁ! ተጠበቁም!" ባላቸው ጊዜ፡ ቃሉ፡ በትክክል ሳይገባቸው ቀርቶ ኖሮ፡ ለሕዝቡ የሚበቃ እንጀራ ባለመያዛቸው፡ የተናገራቸው ስለመሰላቸው፡ "**ምንተ ትሔልዩ በበይናቲክሙ፡ አ ሕፁፃነ-ሃይማኖት? እስመሁ ኅብስት አልብክሙ።**

"እናንት፡ እምነት የጎደላችሁ፡ እንጀራን ስላልያዛችሁ፡ እርስ በርሳችሁ ተጨንቃችሁ የምትነጋገሩት ይህ ነገር፡ ምንድር ነው?" ብሎ፡ በየጊዜያቱ፡ ጥቂቱን ኅብስት እያበረከተ፡ ብዙ ሺህ ሕዝብን ይመግባቸው፥ ከዚያም፡ አያሌ ሌማት ይተርፍ እንደነበረ በማስታወስ፡ "**እፎ ዘኢትሌብዉ፡ ከመ አኮ፡ በእንተ ኅብስት ዘእቤለክሙ፤ 'ዑቁ፥ ወተዐቀቡ፡ እምብኁአሙ ለፈሪሳውያን፥ ወለሰዱቃውያን?'"**

"'‹ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁ! ተጠበቁም!' ያልኋችሁ፡ ስለእንጀራ አለመኾኑን፡ እንዴት ማስተዋል አቃታችሁ?›" ሲል ነቀፋቸው።

**"ወእምዝ ለበዉ አርዳኢሁ፡ ከመ አኮ ዘይቤሎሙ፡ በእንተ ብኅአተ-ኅብስት፡...አላ፡ <u>እምነ ትምህርቶሙ፡ ለፈሪሳውያን፥ ወለሰዱቃውያን!</u>**

"ከዚህ በኋላም፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ <u>ስለፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ትምህርት እንጂ፡</u> ስለእንጀራ እርሾ እንዳልተናገራቸው፡ ያንጊዜ በማስተዋል ገባቸው።"

ከዚህም ጋር፡- **"ወኢይወድዩ ወይነ ሐዲሰ፡ ውስተ ዝቅ ብሉይ፤ ወእመአኮሰ፡ ዝቁ ይነቅዕ፤ ወወይኑሂ ይትከዐው፤ ወዝቁሂ ይትኃጐል። ወባሕቱ፡ ለወይንሰ ሓዲስ፡ ውስተ ዝቅ ሐዲስ፡ ይወድይዎ፤ ወይትዐቀቡ በበይናቲሆሙ ኅቡረ።**

"አዲሱን የወይን-ጠጅ፡ በአሮጌ አቍማዳ አያኖሩም፤ አለዚያ፡ አቍማዳው ይፈነዳል፤ ጠጁም ይፈስሳል፤ አቍማዳውም ይበላሻል። ነገር ግን፡ አዲሱን የወይን-ጠጅ፡ በአዲስ አቍማዳ ያኖሩታል፤ ኹለቱም፡ እርስ በርሳቸው፡ በአንድነት ይጠባበቃሉ።" ያለው መለኮታዊ ቃሉ ነው። (ማቴ. ፱፥ ፲፯፤ ፲፮፥ ፮-፲፪።)

አዎን! እኛም፡ የዛሬዎቹ ሓዋርያት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ይህን የመምህራችንን ማስጠንቀቂያና መመሪያ፡ አጥብቀን አምነንበት፡ በመከተልና በተግባር ላይ በማዋል፡ **<u>"ወይንሰ ሓዲስ። አዲሱ የወይን-ጠጅ"</u> የኾነውን፥ ከዘመናችን ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን የተሳሳተ ትምህርትና ሓሰተኛ ይትበሃል፡** ፍጹም ነጻ ኾኖ፡ በእግዚአብሔርዋ እውነትና ትክክለኛነት፥ ጥራትና ቀናነትም፡ እነሆ፡ ለ፪ሺ፰ (ኹለት ሽህ ስምንት) ዓመታተ-ምሕረት ተጠብቆ፡ ሲለመልምና ሲያፈራ የኖረውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን፡ <u>"ዝቅ ሐዲስ። አዲሱ አቍማዳ</u>" በኾነው ኪዳናዊ ሰውነታችን ተቀብለንና ሞልተን፡ ኢትዮጵያዊ ተልእኳችንና ሓዋርያዊ አገልግሎታችን፡ ይኸው፡ በከፍተኛ ጥንቃቄ እያረጋገጥን፡ በመቀጠል ላይ እንገኛለን።

አንተም፡ የእነዚሁ ፀረ-እግዚአብሔር እና ፀረ-ኢትዮጵያ ወገኖች የኾነውን መጽሓፍ ከተመለከትህ በኋላ፡ በኪዳናዊነትህ፡ *"እውነት የሰዎች ልጆች የሚፈልጉትን በነፃ ፈቃዳቸው ያደርጋሉ? ወይስ የገዢዎቻቸውን ፈቃድ በተጽዕኖ ያደርጋሉ? የሚል ጥያቄም ያስነሳል።"* ላልከው ግምገማህ፡ ይህችን አጭር ሓተታዬን ከመዝጋቴ በፊት፡ በማጠቃለል፡ የምለው ነገር ቢኖር፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡-

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን መሠረት፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውና በእርሱው ቃል፡ "ከእኛ እንደአንዳችን ኾነ!" የተባለው ሰው፡ በፈጣሪው ፈቃድና ልግሥና፡ በሕይወቱና በህልውናው ላይ የተሰጠው የዕውቀት መሥፈርትና የመምረጥ ነጻነት፥ የመወሰን ሥልጣንና የማድረግ ኃይል፡ ወሰን የሌለው ፍጹም ነው፤ ይህም የተፈጥሮ መለኮታዊ ጸጋ፡ በፈጣሪው ጣልቃ-ገብነት እንኳ የማይገሠሥ፣ ከፈጣሪውም በቀር ሌላ የበላይ ገዥ የሌለበት፥ እንደፈጣሪው ኾኖ መኖር እንዲችል ተደርጎ የተፈጠረ መኾኑን ያረጋግጣል።

ስለዚህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥት* ዘንድ ያለው፡ ይህ እምነታችን፡ አበክሮ የሚደግፈው፡ *"የሰው ልጆች የተፈጠሩት፡ አዎን! የሚፈልጉትን* ኹሉ*፥ በነፃ ፈቃዳቸው ሊያደርጉ* እንጂ፡ *የገዢዎቻቸውን ፈቃድ በተጽዕኖ ሊያደርጉ* አይደለም! *"* የሚለውን *ሃይማኖታዊ* ውሳኔ በመኾኑ፡ እኔም፡ ይህንኑ እውነታ በማጽናት፡ ለጥያቄህ፡ ይኸው፡ መልሱን አበርክቼሃለሁ።

በመጨረሻ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥት* ተልእኳችን ውስጥ፡ እንደማንኛውም ሌላው አገልግሎታችን ኹሉ፡ በሥነ-ጽሕፈትም ረገድ፡ ኢትዮጵያዊዉን እግዚአብሔራዊ ሥርዓት ለመጠበቅ፡ የተቻለንን ያህል ስለምንጠነቀቅ፡ በወደፊቱ ጽሑፍህ፡ "*መንግሡት*" የሚለውን ቃል፡ "*መንግሥት*" በሚል የሆሄ አርትዖት እንድታስተካክለው አሳስብሃለሁ።

\+ + +